የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፴
አዲስ አበባ ግንቦት ፴ ቀን ፲፱፻፺፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

13th Year No. 30
ADDIS ABABA 7th June, 2007

<u>ማ ው ጫ</u>

አዋጅ ቁጥር ፭፻፳፯/፲፱፻፺፱ ዓ.ም

በኢኳቶሪያል ጊኒ መንግሥት ጋር የተደረገ የአየር አገልግሎት ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ …. ገጽ ፫ሺ፮፻፲፩

<u>CONTENTS</u>

**Proclamation No. 527/2007**

Government of Equatorial Guinea Air Transport Services Agreement Ratification Proclamation …. Page 3611

**አዋጅ ቁጥር ፭፻፳፯/፲፱፻፺፱**

**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በኢኳቶሪያል ጊኒ መንግሥት መካከል የተደረገ የአየር አገልግሎት <u>ስምምነትን ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ</u>**

የአየር አገልግሎት ለመጀመር የሚያስችል ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በኢኳቶሪያል ጊኒ መንግሥት መካከል እ.ኤ.አ. ታህሣሥ ፲፱ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ስምምነቱ በሥራ ላይ የሚውለው በሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቶቻቸው መሠረት በተዋዋይ ሃገሮች መጽደቁን የሚያረጋግጡ የዲፕሎማቲክ ሰነዶች ልውውጥ ከሚደረግበት ዕለት ጀምሮ እንደሚሆን በስምምነቱ ውስጥ የተመለከተ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፱ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭/፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "ከኢኳቶሪያል ጊኒ መንግሥት ጋር የተደረገ የአየር አገልግሎት ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፭፻፳፯/፲፱፻፺፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**PROCLAMATION NO. 527/2007.**

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE AIR TRANSPORT SERVICES AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF EQUATORIAL GUINEA**

**WHEREAS,** Air Transport Services Agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of Equatorial Guinea was signed in Addis Ababa, on 19th day of December 2005;

**WHEREAS,** it is stipulated in the Agreement that the Agreement shall come into force after the exchange of notes confirming its ratification in compliance with the respective constitutional procedures in force in each country;

WHEREAS, the House of peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session on the 17th day of May, 2007;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution, of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Government of Equatorial Guinea Air Transport Services Agreement Ratification Proclamation No.527/2007."

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ፪. ስምምነቱ ስለመፅደቁ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በኢኳቶሪያል ጊኒ መንግሥት መካከል እ.ኤ.አ. ታህሣሥ ፲፱ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም አዲስ አበባ ላይ የተፈረመው የአየር አገልግሎት ስምምነት ፀድቋል።

## ፫. የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስትር ሥልጣን

የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስትር ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ግንቦት ፴ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 2. Ratification of the Agreement

The Air Transport Services Agreement Signed in Addis Ababa on 19th day of December 2005 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of Equatorial Guinea, is hereby ratified.

## 3. Power of the Minister of Transport and Communications

The Minister of Transport and Communication is here by empowered to undertake all acts necessary for the implementation of the Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall come into force up on Publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 7th day of June, 2007**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**